| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ጽሑፍ ፤ "ብሔረ ፡ ጥበብ ።" |
| ርእስ ፤ | "ምድርና ፡ ኀዋ ።<br>ክፍል ፡ 1 ፤ የፀሓይ ፡ ሥርዐት ።" |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ሚያዝያ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2011-001 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ብሔረ ፡ ጥበብ ።

Universe of Science | Univers de la science

# ምድርና ፡ ኀዋ ።

## ክፍል ፡ 1 ፤ የፀሓይ ፡ ሥርዐት ።

**ኀዋ** ፡ ምድርን ፡ ይከባታል ፤ ወይም ፥ ምድር ፡ ኀዋ ፡ ውስጥ ፡ ትገኛለች ። በምድር ፡ ዙሪያ ፡ ያለው ፡ አየር ፡ ከምድር ፡ በራቀ ፡ መጠን ፡ እየተነነ ፡ ኼዶ ፥ ፈጽሞ ፡ ሲታጣ ፥ ያን ፡ ጊዜ ፡ ኀዋ ፡ የሚባለው ፡ ይዠምራል ። ኀዋ ፥ አየር ፡ አይኑርበት ፡ እንጂ ፥ ባዶ ፡ አይደለም ፤ እንዲያውም ፡ በመጠን ፡ ከምድር ፡ እጅጉን ፡ የሚበላልጡ ፥ ቍጥራቸው ፡ የማይታወቅ ፡ ሌሎች ፡ ዓለሞችና ፡ ከዋክብት ፡ ይገኙበታል ።

ፀሓይ ፡ ከከዋክብት ፡ ዅሉ ፡ ለምድር ፡ የቀረበችዋ ፡ ኮከብ ፡ ነች ። ለምድር ፡ ስለ ፡ ቀረበችም ፥ ከሌሎቹ ፡ ከዋክብት ፡ ይልቅ ፡ ብርሃኗ ፡ በልጦ ፡ ይታየናል ። ፀሓይ ፡ እንደ ፡ ምድራችን ፡ ጥጥር ፡ አይደለችም ፤ እውስጧ ፡ ባለው ፡ **ጕልበት** ፥ ዙሪያ ፡ ገባዋን ፡ የከበባትን ፡ **ንዛዥ** ፡ ወይም ፡ *"ጋዝ"* ፡ (gas | gaz) ፡ በማንደዷ ፡ እንደእሳት ፡ ኳስ ፡ ኾና ፥ ጕልበቷን ፡ ወደ ፡ ብርሃንና ፡ ሙቀት ፡ ለውጣ ፡ ላካባቢዋ ፡ ትሰጣቸዋለች ። የገጿ ፡ ትኵሳት ፡ 6000 ፡ **ደረጃ** ፡ ይደርሳል ።

ውሃን ፡ የታደለች ፡ ምድራችንም ፥ የፀሓይን ፡ ብርሃንና ፡ ሙቀት ፡ በማግኘቷ ፡ ሕያውት ፡ ኾናለች ፤ ከዕፀዋት ፡ ሌላ ፥ ሰውን ፡ ጨምሮ ፥ ነፍሳት ፡ በያይነቱ ፡ ይኖሩባታል ።

ምድራችንን ፡ የምታውደዋ ፡ ጨረቃም ፥ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፥ ከፀሓይ ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ አንጻር ፡ ስትሰለፍ ፥ በምድራችን ፡ ላይ ፡ የፀሓይ ፡ **ግርዶሽ** ፡ ይከሠታል ። ስናመጣጥናቸው ፥ ፀሓይ ፡ የእግር ፡ ኳስን ፡ ታኽላለች ፡ ብንል ፥ ምድር ፡ አንድ ፡ ዐተርን ፥ ጨረቃ ፡ ደግሞ ፡ የመርፌ ፡ ጫፍን ፡ ያኽላሉ ።

ፀሓይ ፡ ዙሪያዋን ፡ በሚያውዱ ፡ ዘጠኝ ፡ **ተንዣባቢዎች** ፡ ታጅባለች ፤ ምድርም ፡ አንዷ ፡ ተንዣባቢት ፡ ናት ። ዐሥሩ ፡ አንድጋ ፡ **ሥርዐተ ፡ ፀሓይ** ፡ (solar system | système solaire) ፡ ይባላሉ ። **ስሕበት** ፡ የተባለው ፡ ምስጢራዊ ፡ ኀይል ፡ ተንዣባቢዎቹን ፡ ከፀሓይ ፡ ጋራ ፡ ያሳስባቸዋል ፥ ያጣብቃቸዋል ። ይሄው ፡ ስሕበት ፡ እኛንም ፡ ከምድር ፡ ጋራ ፡ አዋዶ ፡ ይይዘናል ።

ምድራችን ፡ ከፀሓይ ፡ ብዙም ፡ ሳትቀርብ ፥ ብዙም ፡ ሳትርቅ ፥ አማካይ ፡ ወይም ፡ ተስማሚ ፡ ርቀት ፡ ላይ ፡ በመገኘቷ ፥ ከዘጠኙ ፡ ተንዣባቢዎች ፡ ይልቅ ፡ ሕይወት ፡ ያለባት ፡ ምድረ ፡ ገነት ፡ ኾናለች ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ አበላሻት ፡ እንጂ ። ለፀሓይ ፡ ከቀረበው ፡ ስንነሣ ፥ ዘጠኙ ፡ ተንዣባቢዎች ፡ በቅደም ፡ ተከተላቸው ፡— ***መርኩሪ ፣ ቬኑስ ፣ ምድር ፣ ማርስ ፣ ጁፒተር ፣ ሳቱርን ፣ ዑራኑስ ፣ ኔፕቱን ፣ ፕሉቶ*** ፡ ናቸው ። እያንዳንዳቸው ፡ የየራሳቸው ፡ ጨረቃዎች ፡ አሏቸው ። ከፀሓይ ፡ በመራቃቸው ፡ አንጻር ፡ ዑደታቸው ፡ ስለሚለያይ ፥ ዓመታቸውም ፡ ይለያያል ። ለምሳሌ ፥ የምድር ፡ ዓመት ፡ 365 ፡ ቀናት ፡ ሲኾን ፥ ለፀሓይ ፡ ቀረብ ፡ ያለችዋ ፡ የቬኑስ ፡ ዓመት ፡ 225 ፡ ቀናት ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ የማርስ ፡ ደግሞ ፥ ራቅ ፡ በማለቷ ፥ 687 ፡ ቀናት ፡ ነው ፨


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።